# የኢትዮጵያ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት

## የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያ 6 ወር

## ዕቅድ አፈፃፀም

ጥር 2014 ዓ.ም

ኢ.ው.ቴ.ኢ

መግቢያ .......... 2
1. የዝግጅት ምዕራፍ ተግባራት አፈጻጸም .......... 2
1.1. የውስጥ አቅም ግንባታ .......... 2
1.2. የኢንስቲትዩቱ ራዕይ፣ ተልዕኮና ዕሴቶች .......... 3
2. የትግበራ ምዕራፍ ተግባራት አፈፃፀም .......... 4
2.1. የቁልፍ ተግባራት አፈጻጸም .......... 4
2.2. የዐበይት ተግባራት አፈጻጸም .......... 4
2.2.1. አጫጭር ተግባር-ተኮር ስልጠና አፈፃፀም .......... 4
2.2.2. ለቴ/ሙ/ት/ስልጠና ተቋማት የተሰጠ ቴክኒካል ድጋፍ .......... 5
2.2.3. የሙያ ብቃት ምዘና ተግባራት አፈጻጸም .......... 6
2.2.4. የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር አፈፃፀም .......... 7
2.2.5. ስፔሻላይዝድ ላቦራቶሪ አገልግሎት ተግባራት አፈፃፀም .......... 8
2.3. የፕሮጀክቶች አፈፃፀም .......... 8
2.3.1. በመንግስት የሚሰሩ ፕሮጀክቶች .......... 8
2.3.2. በዕርዳታ የሚሰሩ ፕሮጀክቶች .......... 9
2.4. የቅንጅታዊ አሰራር ተግባራት አፈጻጸም .......... 10
2.5. የድጋፍ አገልግሎት ሥራዎች አፈጻጸም .......... 12
2.6. የበጀት አፈፃፀም .......... 16
3. የማጠቃለያ ምዕራፍ አፈጻጸም .......... 17
3.1. የድጋፍ አሰጣጥ አፈጻጸም .......... 17
3.2. ተቋማዊ ጠንካራና ደካማ ጎኖች .......... 18
3.3. ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች .......... 19
የበጀት አፈፃፀም በሠንጠረዥ .......... 20
የመደበኛ በጀት አፈፃፀም .......... 20
የካፒታል በጀት አፈፃፀም .......... 21

## መግቢያ

ኢንስቲትዩቱ ተልዕኮውን ለማሳካት በ2014 በጀት ዓመት ያቀዳቸው ዋና ዋና ተግባራት የለውጥ ሰራዊት ግንባታ እና የማስፈፀምና የመፈፀም አቅም በማጠናከር ለዘርፉ ባለሙያዎች አጫጭር ተግባር-ተኮር ስልጠናዎችን መስጠትና በቴክኒካል የመደገፍ እና የብቃት ምዘና ማዕከል አገልግሎት መስጠት ነው፡፡ እንዲሁም ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችን በማላመድ ማሸጋገር፣ ጥናት እና ምርምር ማካሄድ እና ስፔሻላይዝድ ላቦራቶሪን የማደራጀትና ዓለም አቀፍ ዕውቅና እንዲኖረው የማድረግ ሥራዎች ናቸው፡፡ ተቋሙም ተልዕኮውን ለማሳካት በአራት ዓላማ አስፈፃሚዎች እና ዘጠኝ ደጋፊ የስራ ሂደቶች የተዋቀረ ሲሆን፣ አሁን ያለው አጠቃላይ የሰው ኃይል 202 (ወንድ 123፣ ሴት 79) ነው፡፡

በዚሁ መሰረት የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያ 6 ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት የሚያካትታቸው የዝግጅት፣ የትግበራ እና የማጠቃለያ ምዕራፍ ዕቅድ አፈፃፀም ዝርዝር ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 1. የዝግጅት ምዕራፍ ተግባራት አፈጻጸም

#### 1.1. የውስጥ አቅም ግንባታ

- በ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም የሁኔታዎች ግምገማ በማድረግ በአፈፃፀም የተገኙ ውጤቶች፣ የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች መልካም ተሞክሮዎች እና የበጀት ዓመቱን ቁልፍ ችግሮች በመለየት ለ2014 ዕቅድ ግብዓት እንዲሆን ተደርጓል፣
- በአፈፃፀም ወቅት የሚታዩ ችግሮች የሚፈቱበት እና ከዕቅድ አንፃር የአፈፃፀም ደረጃ የሚለይበት የክትትልና ግምገማ ስርዓት በመፍጠር እየተሰራ ነው፣
- የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ላይ በየደረጃው ካሉ ሰራተኞች ጋር ውይይት በማድረግ በዕቅዶቹ ላይ የጋራ ግንዛቤ ተፈጥሯል፣
- ለ53 (ወንድ 26፣ ሴት 27) ጥበቃና ፅዳት ሰራተኞቻችን የ2 ቀን ስልጠና እንዲያገኙ ተድርጓል፣
- ለ199 (ወንድ 116. ሴት 83) ሠራተኞች በመንግሥት የሰው ሃብት ሕጎችና ፍኖተ ካርታ ላይ የሁለት ቀን ስልጠና እንዲሰጠዋ ተደርጓል፣
- ለ15 (ወንድ 11፣ ሴት 4) ሠራተኞች በተቀናጀ የሰው ሃብት መረጃ አያያዝ (IFMIS) ላይ ሥልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፣

- በመንግስት ግዥ መመሪያ ላይ የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ፣ የግዥ ባለሙያዎችና ከግዥ ጋር ግንኙነት ያላቸው 13 (ወንድ 11፣ ሴት 2) አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል
- በአጠቃላይ እስከ 6 ወራት ድረስ 267 (ወንድ 153፣ ሴት 114) ሰራተኞች በተለያየ ዙር የአጭር ጊዜ አቅም ግንባታ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፣
- የስፔሻላይዝድ ላቦራቶሪ አደረጃጀትን በማጠናከር የሚጠበቀውን አገልግሎት ለመስጠት እንዲያስችል አዲስ የአደረጃጀት ሠነድ ተዘጋጅቶ እንዲፈቀድ ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በተላከው መሰረት ተፈቅዷል፣

## 1.2. የኢንስቲትዩቱ ራዕይ፣ ተልዕኮና ዕሴቶች

### ተልዕኮ

በሀገሪቱ በውሃው ዘርፍ ፈጣን ልማት ለማምጣት የሚያስችል የሰው ሃይል አቅምን ማጎልበት፣ በጥናትና ምርምር የቴክኖሎጂ ሽግግር ማምጣት እና የስፔሻላይዝድ ላቦራቶሪና የሙያ ብቃት ምዘና አገልግሎት በመስጠት የዘርፉን የመፈፀም አቅም ማሳደግ፣

### ራዕይ

ኢንስቲትዩቱ በ2022 በምሥራቅ አፍሪካ በውሃው ዘርፍ በአቅም ግንባታና ቴክኖሎጂ ሽግግር የልህቀት ማዕከል ሆኖ ማየት!

### ዕሴቶች

- ሁልጊዜ መማር፣
- ፈጠራ፣
- ጥራትና ተቀባይነት፣
- ግልፅነትና ተጠያቂነት፣
- የቡድን ሥራ፣
- ሙስናንና ብልሹ አሠራርን መፀየፍ፣
- አሳታፊነት፣
- አገልጋይነት፣
- ለለውጥ መሥራት፣

## 2. የትግበራ ምዕራፍ ተግባራት አፈፃፀም

ኢንስቲትዩቱ በዝግጅት ምዕራፍ የሚሰሩ ተግባራትን በመፈጸም ወደ ትግበራ ምዕራፍ በመግባት የተከናወኑ ተግባራት አፈፃፀም እና የተገኙ ውጤቶች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 2.1. የቁልፍ ተግባራት አፈጻጸም

**የለወጥ ማሪያዎች ትግበራ አፈጻጸም**

ኢንስቲትዩቱ ከተሰጠው ተልዕኮ አንጻር የሚጠበቀውን ውጤት ለማስመዝገብ እና የአገልግሎት አሰጣጥ ቅልጥፍናን ለማሻሻል የተሰሩ የለውጥ መሣሪያዎች ተግባራት፡-

- የተግባራት አፈፃፀም በመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት አገልግሎት ለባለድርሻ አካላትና ተገልጋዮች እየተሰጠ ነው፣
- በየደረጃ የሚዘጋጁ ዕቅዶች በተከለሰው ሚዛናዊ ውጤት-ተኮር ስርዓት መሰረት በማድረግ ተግባራት ለፈፃሚ እንዲወርድ (cascade) ተደርጎ እየተሰራበት ይገኛል፣
- በተዘጋጀው የዜጎች ቻርተር መሰረት ለተገልጋዮች አገልግሎት እየተሰጠ ነው፣
- የካይዘን ፍልስፍና ትግበራ በሁሉም የሥራ ክፍሎች እየተሰራበት ይገኛል፣

**በተሰሩ የለውጥ ሥራዎች የተገኙ ውጤቶች፡-**

- የለውጥ ሠራዊት የሚመራባቸውን መርሆዎችን (በቡድን መስራት፣ በተከታታይነት ሥራን መገምገምና ዕለታዊ እርስ-በርስ የመረጃ ልውውጥ) ሥራ ተግባራዊ ተደርጓል፣
- ሥራዎችን በጋራ የማቀድና የመፈፀም ባህል ተፈጥሮ እየተሰራበት ይገኛል፣
- እርስ-በእርስ የመማማርና አቅም የመገነባባት ባህል በመዳበሩ በፈፃሚው መካከል ተቀራራቢ የመፈጸም አቅም ለመፍጠር ተችሏል፣
- ሥራን ቆጥሮ የመስጠትና ቆጥሮ የመቀበል ሥራ ተሰርቷል፣ እየተሰራም ይገኛል፣

**ከህዝብ ክንፍ ጋር የተከናወኑ ተግባራት አፈፃፀም**

ከባለድርሻ አካላት ጋር በየሶስት ወራት የሚደረገውን ውይይት አጠቃላይ የተቋሙ ተልዕኮ ዙሪያ እና በ10 ዓመት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ላይ ውይይት ለማድረግ በዝግጅት ላይ ነው፡፡

### 2.2. የዐበይት ተግባራት አፈጻጸም

#### 2.2.1. አጫጭር ተግባር-ተኮር ስልጠና አፈፃፀም

- ለአምስት ነባር የስልጠናና የማስተማሪያ መሳሪያዎች /TTLM/ የመከለስና የማሻሻል ሥራ:-
    - Gen-set Operation and Maintenance

- o GIS & Remote Sensing
- o Drilling Supervision
- o Water Supply Engineering and
- o Non-revenue Water management (NRW) ለቅይጥ የስልጠና ዘዴ (Blended training Approach) እንዲሆን የተሻሻሉ ኮርሶች ናቸው፡፡

- ➢ ዓመታዊ የስልጠና መርሃ-ግብር በማዘጋጀት ለባለድርሻ አካላት በማሰራጨት የማስተዋወቅ ሥራ ተሰርቷል፣
- ➢ ለ772 የዘርፉ ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ በአራት የስልጠና መስኮች፡-
  - o በውሃ ሀብት ልማትና ቁፋሮ ቴክኖሎጂ 172 ሰልጣኞች፣
  - o በኤሌክትሮ-ሜካኒካልና የቁፋሮ መሳሪያዎች ጥገና ቴክኖሎጂ 90 ሰልጣኞች፣
  - o በመጠጥ ውሃ ሳኒቴሽን ምህንድስና ቴክኖሎጂ 142 ሰልጣኞች፣
  - o በመስኖና ድሬኔጅ ምህንድስና ቴክኖሎጂ 73 ሰልጣኞች፣
  - o ታዳሽ ኃይል ልማት ቴክኖሎጂ ዲፓርትመንት 22 ሰልጣኞች፣

በድምሩ ለ499 (ወንድ 413፣ ሴት 86) 65% የዘርፉ ባለሙያዎች በ5 የስልጠና ዘርፍ እና በ24 የዘርፉ የስልጠና ኮርሶች አጫጭር ተግባር-ተኮር ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ አፈፃፀሙ ከባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር ስልጠና የወሰዱ ባለሙዎች በቁጥር በ140 ብልጫ አለው፡፡

### 2.2.2. ለቴ/ሙ/ት/ስልጠና ተቋማት የተሰጠ ቴክኒካል ድጋፍ

- ➢ በዚህ 6 ወራት ለ150 የቴ/ሙ/ት/ስ ተቋማት አሰልጣኞችና ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ቴክኒካል ድጋፍ ለመስጠት ታቅዶ፡-
  - o በሙያ ደረጃ አዘገጃጀት ለ24 (ወንድ) ቴ/ሙ/ት/ስ/ተቋማት አሰልጣኞች የአቅም ግንባታ ቴክኒካል ድጋፍ ስልጠና ተሰጥቷል፣
  - o በካሪኩለም አዘገጃጀት ላይ ለ15 (ወንድ 14 ሴት 1) ኮሌጅ አሰልጣኞች ባለሞያዎች ሥልጠና ተሰጥቷል፣
  - o የኢንተርንፕረነርሽፕ ማስተማሪያ ሞጁል አዘገጃጀት ላይ ለ7 (ወንድ) የኮሌጅ አሰልጣኞች እና ባለሞያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፣
  - o በውሃ አቅርቦት፣ በኤሌክትሮ-ሜካኒካል እና በመስኖና ድሬነጅ ሞያዎች በTTLM አዘገጃጀት ላይ ለ18 (ወንድ 15 ሴት 3) አሰልጣኞች የሥልጠና ቴክኒካል ድጋፍ ተሰጥቷል፣
  - o በጥናትና ምርምር ሥነ-ዘዴ እና በፕሮጀክት ፕሮፖዛል አዘገጃጀት ላይ በደቡብ ክልልና በሲዳማ ክልል ከሚገኙ በውሃ ዘርፍ ስልጠና ከሚሰጡ ቴክኒክና ሞያ ኮሌጆች ለተውጣጡ ለ25

(ወንድ 23 ሴት 2) አሚሮች በወልቂጤ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ የአቅም ግንባታ ቴክኒካል ድጋፍ ተሰጥቷል፣

- በትብብር ሥልጠና አተገባበር ላይ በደቡብ ክልልና በሲዳማ ክልል ከሚኙ በውሃ ዘርፍ ስልጠና ከሚሰጡ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ለተውጣጡ ለ25 (ወንድ 23 ሴት 2) አሚሮችና አሰልጣኞች በወልቂጤ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ የአቅም ግንባታ ቴክኒካል ድጋፍ ተሰጥቷል፣
- የእሴት ሰንሰለት ሥልጠና ለ27 (ወንድ) አሰልጣኞች የአቅም ግንባታ ቴክኒካል ድጋፍ ተሰጥቷል፣ –

በአጠቃላይ በውሃው ዘርፍ ሙያዎች ስልጠና ለሚሰጡ የቴ/ሙ/ት/ስልጠና ተቋማት ለ141 (133 ወንድ፣ 8 ሴት) 94% አሰልጣኞች የአቅም ግንባታ ቴክኒካል ድጋፍ ስልጠና ተሰዋቷል፡፡ አፈፃፀሙ ከባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የአቅም ግንባታ ቴክኒካል ድጋፍ ያገኙ ባለሙዎች በቁጥር በ40 ብልጫ አለው፡፡

### 2.2.3. የሙያ ብቃት ምዘና ተግባራት አፈጻጸም

- ለ250 ባለድርሻ አካላት ባለሙያዎች በሙያ ብቃት ምዘና አገልግሎት ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ258 (ወንድ 224 ሴት 34) በሙያ ብቃት ምዘና አስፈላጊነትና ሂደት ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ አፈፃፀሙ ከዕቅድ በላይ ነው፣
- የምዘና ማዕከልን በሶስት ሙያዎች (በውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን፣ በመስኖና ድሬኔጅ፣ በሶላር ኢነርጂ) ሙያዎች የምዘና ግብአቶችን ለማሟላት በታቀደው መሰረት ለምዘና የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በሶስቱም ሙያዎች በዓይነት በመለየት የግዥ ፍላጎት ቀርቦ ግዥ ለመፈፀም በሂደት ላይ ነው፣
- በ6 ወራት ለ80 የዘርፉ ባለሙያዎች የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከል አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ በኤሌክትሮ-ሜካኒካል ሙያ እና በመጠጥ ውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን ሙያ ከደረጃ I-III ባሉት ላይ ለ94 (ወንድ 75፣ ሴት 19) የዘርፉ ባለሙያዎች የሙያ ብቃት ምዘና አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ አፈፃፀሙ ከመቶ ፐርሰንት በላይ ሲሆን፣ ከባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የሙያ ብቃት ምዘና ያገኙ ባለሙዎች በቁጥር በ84 ብልጫ አለው፡፡

### 2.2.4. የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር አፈፃፀም

- ምርምርን በተመለከተ፡-
  - የምርምር ገምጋሚ ኮሚቴ የውስጥ አሰራር መመሪያ በተሰጡ አስተያየቶች ላይ ማስተካከያ በማድረግ በስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፣
  - በዚህ በጀት ዓመት ለሚጀመሩ 5 ምርምሮች የምርምር ርዕሶችን በመለየት ከምርምር ስራው የሚጠበቅ ውጤት ለተመራማሪዎች ግልፅ በሆነ መልኩ ተዘጋጅቷል፡፡ እንዲሁም የጥሪ ማቴሪያል በማዘጋጀት የምርምር ጥሪ (Call for the Proposal) ለተመራማሪዎች የቀረበ በመሆኑ የሚቀርቡ የምርምር ፕሮፖዛሎችን ለማስገምገም ከገምጋሚዎች ጋር የአገልግሎት ስምምነት ሰነድ ተዘጋጅቶ ተፈርሟል፡፡ 15 ተወዳዳሪ የምርምር ፕሮፖዛሎች ቀርበው 5ቱን ለመለየት እየተሰራ ነው፡ ከተያዘው ዕቅድ አንፃር አፈፃፀሙ 100% ነው፡፡
  - በ2013 በጀት ዓመት 2 በውስጥ ባለሙያዎችና 2 በውጭ ተመራማሪዎች የተጀመሩ ምርምሮችን በመርሃ-ግብሩ መሰረት እንዲጠናቀቁ ለማድረግ ክትትልና ግምገማ በማድረግ የምርምር ስራው ያለበትን ደረጃ በመለየት ድጋፍ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በ2012 የተላለፉ ምርምሮች እንዲጠናቀቁ በተደረገው ክትትልና ድጋፍ መሰረት 3 ምርምሮች ተጠናቀው "Final Draft Report" የቀረበ በመሆኑ ከግብዓት ማሰባሰቢያ መድረክ በኃላ የምርምሮችን ውጤት ሥራ ላይ ለማዋል እየተሰራ ነው፡፡
- ቴክኖሎጂ ሽግግርን በተመለከተ፡-
  - በምስራቅ ሸዋ ዞን ደንካካ ቀበሌ 300 የአካባቢ ነዋሪዎችን ተጠቃሚ ያደረገ ስድስት ወጪ ቆጣቢ የውሃ ጉርጓዶችን በመቆፈርና አራት አይነት የውሃ ፓምፖችን (ሶላር፣ አክሰስ፣ ሮፕ እና ኤማስ) ለህብረተሰቡ በማስተላፍ፡-
    1. የህብረተሰቡን የውሀ አቅርቦት ችግር መፍታት ተችሏል፣
    2. የሶላር ሀይልን በመጠቀም አማካይ በሆኑ ቦታዎች ህብረተሰቡ የመብራት አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ተችሏል፣
    3. የአካባቢው ህብረተሰብ ከብቶች ውሃ የማግኘት ችግርን ለመፍታት የውሃ ገንዳ በመስራት በሶላር ፓምፕ ውሃ እንዲቀርብ ተደርጓል፣
  - በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚተገበረውን የዝናብ ውሃን በስበት ሀይል፣ የተለያዩ ፓምፖችን የመጠቀም ዘዴ ዲዛይን ተዘጋጅቶ የፓይለት ሙከራ በኢንስቲትዩቱ ግቢ ለመትከል እየተሰራ ይገኛል፡፡

### 2.2.5. ስፔሻላይዝድ ላቦራቶሪ አገልግሎት ተግባራት አፈፃፀም

- በበጀት አመቱ 75 ናሙናዎች ላይ በተለያዩ ፓራሜትሮች ላይ ለሚካሄደው ፍተሻ አገልግሎት ተጠቃሚዎች እንዲያውቁት ስፔሻላይዝድ ላቦራቶሪ የሚሰጣቸው አገልግሎቶችን የማስተዋወቅና ፍላጎታቸውን የመቀበል ስራ፣ በአራት ክልሎችና በሁለት የከተማ አስተዳደር መጠጥ ውሃ ላቦራቶሪዎች ፍላጎታቸውን የመለየት እና ተቋሙ የሚሰጣቸውን የላቦራቶሪ አገልግሎቶች የማስተዋወቅ ስራ ተሰርቶ ሪፖርቱ ተዘጋጅቷል፡፡ ከተያዘው ዕቅድ አንፃር አፈፃፀሙ100% ነው፡
- ሁለት የላቦራቶሪ ኦፔሬሽናል ማኑዋል ለማዘጋጀት ታቅዶ አንድ የፊዚኮ-ኬሚካል እና አንድ የማይክሮ-ባዮሎጂ ኦፔሬሽናል ማኑዋሎች (100%) ተዘጋጅተዋል ፣
- አምስት የላቦራቶሪ ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ አራት (80%) ባለሙያዎች ስልጠናውን እየተከታተሉ ይገኛሉ፣

## 2.3. የፕሮጀክቶች አፈፃፀም

### 2.3.1. በመንግስት የሚሰሩ ፕሮጀክቶች

**ሀ. የስፔሻላይዝድ ላቦራቶሪ ህንጻ ግንባታ፡-**

- የግንባታ ቁጥጥርና የውል አስተዳደር ሥራ እና የዲዛይን ግምገማ መንግስታዊ የልማት ድርጅት በሆነው የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ዲዛይንና ሱፐርቪዥን ሥራዎች ኮርፖሬሽን የሕንፃና ከተማ ዲዛይንና ቁጥጥር ሥራዎች ዘርፍ እየተሰራ ነው፣
- የግንባታው ፊዚካል ሥራ ዕቅድ 100% ሲሆን፣ አጠቃላይ ፊዚካል ክንውኑ ከመጀመሪያው ዕቅድ አንፃር 99.39% ሲሆን፣ በአማካሪ ድርጅት የግንባታ ዲዛይን ለውጥ ምክንያት ተጨማሪ ሥራ ከተሰጠው ጋር ሲነፃፀር አጠቃላይ የፊዚካል ሥራው አፈፃፀም 87% ነው፣
- የለቦራቶሪ ፈርኒቸር ግዥ ለመፈፀም ግልፅ ጨረታ በጋዜጣ ወጥቶ የጨረታ ሰነዱ በግምገማ ላይ ይገኛል፣

**ለ. የማስተማሪያና የስልጠና ፋሲሊቲዎች ግንባታ**

- የመማሪያ ክፍሎች ዕድሳት (Class Room Renovation) ግንባታ ቴኒስ ሜዳ ፊዚካል ሥራ 100% ለማጠናቀቅ ታቅዶ አጠቃላይ ፊዚካል አፈፃፀሙ 75% ላይ ይገኛል፡፡ የአፈፃፀም ማነስ የታየበት ምክንያት ኮንትራክተሩ በግል ችግር ሥራውን አቋርጦ ስለነበረና በቅርብ ሥራውን በመጀመሩ ነው፡፡
- የግቢው አጥር ግንባታ በወጣው ግልፅ ጨረታ መሰረት በአሸናፊ ሥራ ተቋራጭ ግንባታው እየተከናወነ ሲሆን፣ አፈፃፀሙም 20 ፐርሰንት ላይ ይገኛል፡፡

### 2.3.2. በዕርዳታ የሚሰሩ ፕሮጀክቶች

#### 2.3.2.1. በሞሮኮ ንጉስ መሀመድ 6ኛ የዘላቂ ልማት ፋውንዴሽን የሚገነባው የስልጠና ፋሲሊቲ ህንፃ ግንባታ፡-

- በ136.96 ሚሊዮን ብር በውጭ ዕርዳታ የሚገነባው ህንፃ፣ በአጫጭር ስልጠና አቅም ግንባታ እና ለማዕከሉ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች አቅርቦት የሚያጠቃልል ሲሆን፣

**ግንባታን በተመለከተ**

- አንድ ህንፃ G+1 (ለቢሮ አገልግሎት፣ ለመማሪያ ክፍሎች፣ ለስብሰባ አደራሽ፣ ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ) አገልግሎት የሚውሉ ክፍሎች፣
- ሶስት ዎርክ-ሾፖች (Water and waste water treatment, Irrigation system, Electricity, Electromechanical and Renewable energies)
- ሁለት ላቦራቶሪዎች (Water Physico-Chemical, Microbiological) እና
- ማስተማሪያ ፋርም (open field, Greenhouse, and Shade house) ጠቅላላ 2,640 ሜ2 ላይ ያረፈ ግንባታ በኮቪድ ምክንያት የዘገየ ቢሆንም፣ አጠቃላይ የፊዚካል ሥራ አፈፃፀም 100% ላይ ነው፣

**የመሳሪያዎች አቅርቦት**

- ለስልጠና ማዕከሉ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች በሙሉ ለዎርክ-ሾፕ በተገነቡ ህንፃዎች ውስጥ የገቡ ሲሆን፣ የኢንስታሌሽን ሥራ በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት የዘገየ ሥራ ነው፡፡

#### 2.3.2.2. በጃይካ የሚደገፍ training operation and management ፕሮጀክት

- E-learning ስልጠና መስጠት የሚያስችል የ 5 TTLM ዝግጅት ላይ ለባለሙያዎቻችን የሥራ ላይ አቅም ግንባታ ሥራ ተከናውኖዋል፣
- ለ12 የኢንስቲትዩቱ ከፍተኛ እና መካከለኛ አመራሮች መሠረታዊ የአመራር ዕውቀት ማጎልበቻ ስልጠና ተስጥቷል፣
- የጃፓን ዓለም-አቀፍ ትብብር ኤጄንሲ (JICA) በ"training operation and management" ፕሮጀክት ማዕቀፍ ጥልቀት ያለው የውሃ ጉድጓድ መቆፈር የሚችል አንድ የውሃ ጉድጓድ መቆፈሪያ ሪግ እና የመለዋወጫዎቹን ግዥ ለመፈፀም ከተቋማችን ጋር በተገባው ውል መሰረት ግዥው ተካሂዶ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት በፋብሪካ እየተመረተ ይገኛል፡፡

## 2.4. የቅንጅታዊ አሰራር ተግባራት አፈጻጸም

ኢንስቲትዩታችን ተልዕኮውን ለማሳካት ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር ቅንጅት በመፍጠር የሚከተሉት ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

### 2.4.1. መንግስታዊ ተቋማት

- ለ70 የተመረጡ የከተማ የውሃ አገልግሎቶች ባለሙያዎች (In-service refreshment training On Distribution Systems and Electro-mechanical Equipment's Operation & Maintenance) ስልጠና ለመስጠት ቅድመ-ሁኔታዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፣
- ከመስኖ ልማት ኮሚሽን ጋር ለ34786 ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት የሚያስችል የአምስት ዓመት ስምምነት የተፈራረምን ሲሆን፣ በተፈራረምነው መሰረት ለ40 ባለሙያዎች ስልጠና የተሰጠ ሲሆን፣ ስልጠናውን በስፋት ለመጀመር በስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት "Gap servay" ለመለየት ጥናት እየተካሄደ ይገኛል፣
- ለታላቁ ቤተ-መንግስት የአንድነት ፓርክ 11 ባለሙያዎች "Switch Board and Chiller Operation and Maintenance" ላይ በተግባር የተደገፈ ስልጠና ተሰጥቷል፣
- ለሶማሊ ክልል ውሃ ቢሮ ከ20 ወረዳዎች የውኃ አገልግሎት ተቋማት ለተውጣጡ 20 ባለሙያዎች በኦፕሬሽንና ጥገና እና ፕሮጀክት አሰተዳደር ላይ የ21 ቀናት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- ከፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ፣ ከADRA ኢትዮጵያ እና ከጃፓይካ ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር በአራት የሙያ ደረጃዎች (በውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን፣ በመስኖና ድሬኔጅ፣ በኤሌክትሮ-ሜካኒካል እና በሶላር PV ኢንስታሌሽን እና ኦፕሬሽን ሙያዎች በአተገባበር ላይ የታዩ ክፍተቶች እና አዲሱ የቴክኒክና ሙያ ፖሊሲና ስትራቴጂን መሰረት በማድረግ የሙያ ደረጃ እንዲከለስ ተደርጓል፣
- ከፌደራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ እና ADRA Ethiopia ጋር በመተባበር የኢንተርፕሪነርሽፕ ክህሎት ማሰልጠኛ 2 ሞጁሎች ተዘጋጅተው በሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፣

### 2.4.2. መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች

- ከIRC-WASH በጋራ ሊያሰራን የሚችል ዓመታዊ ዕቅድ በማዘጋጀት Blended Learning System (E-learning & Face to face) የስልጠና ዘዴ በሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ እንዲከለስ ተደርጎ ስልጠና እየተሰጠ ይገኛል፡፡ ለአንድ የኢንስቲትዩቱ አመራር እና አንድ ባለሙያ የልምድ ልውውጥ እና ጉብኝት ዕድል በኔዘርላንድ ሀገር እንዲያገኙ ተደርጓል፣

- ከ "Water-Aid Ethiopia" ጋር የአምስት ዓመት የመግባቢያ ሰነድ በተፈረረምው መሰረት ከኦሮሚያና አማራ ክልል 23 ከተሞች ለተወጣጡ 129 ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት ተችሏል፡፡ እንዲሁም 17 የስልጠና ሞጁሎች የመከለስ ሥራ የተጠናቀቀ በመሆኑ ከሌላ SCRS-WASH ጋር ስልጠና እንደንሰጥ ደርጅቱ እያማከተ ይገኛል፣
- ከ UNICEF ጋር በመሆን ለሶማሌ ክልል፣ ለአፋር ክልል እና ለአማራ ክልል "Multi Village Water Supply Scheme Operation, Maintenance and Administration" እና POST CONSTRUCTION MANAGEMENT and WATER WELL DRILLING CAPACITY DEVELOPMENT SUPPORT FOR SAFE & SUSTAINABLE WATER SUPPLY SERVICE ፕሮጀክት ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና ለመስጠት የሚያስችል የድጋፍ ስምምነት ተጠናቆ ሥራው በሶማሌ ክልል የተጀመረ ሲሆን፣ በሌሎች ክልሎችም ለማስጀመር በሂደት ላይ ነው፡
- ከፕላን ኢንተርናሽናል-ኢትዮጵያ ጋር በመሆን በደቡብ እና ጋምቤላ ክልል ወጣቶችን ወደ ሥራ ለማስገባት የሚያስችል implementation of Youth Economic Empowerment (YEE) የሚል ፕሮጀክትን ለመተግበር በተፈራረምነው ውል መሰረት ለስልጠና ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የስልጠና የሶላር ላቦራቶሪ ዕድሳትና ግብዓት የማሟላት ሥራ በጀት ተመድቦ እየተሰራ ይገኛል፡፡ እንዲሁም ለኢንስቲትዩቱ የሶላር ላብ የሚያገለግሉ መሣሪያዎች በ19022 ዩሮ ተገዝቶ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ሲሆን፣ በሶላር ላይ በጋራ ስልጠና ለመስጠት የካሪኩለም ዝግጅት ሥራ ተከናውኗል፣
- ከ GIZ ጋር በመሆን ለዘርፉ ባለሙያዎች በsolar-powered irrigation system ላይ ስልጠና ለመስጠት ሁለት የኢንስቲትዩታችን ባለሙያዎች የአሰልጣኝነት ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጎ ከጥር ወር 2014 በጀት ዓመት ጀምሮ ለ80 የዘርፉ ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት ፕሮግራም ተይዟል፣
- ከPeople in Need ጋር ስትራቴጂክ የጋራ መግባቢያ ሰነድ በተፈረረምው መሰረት ከደርጋ-ዓለም ከተማ ውሃ አገልግሎት አራት ባለሙያዎች በ"Pump, Geneset and Switch board operation & Maintenance" ላይ ለሃያ ቀናት ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል፣
- ከ "water witness international" ጋር በመሆን በውሃው ዘርፍ በዕውቀት ላይ የተመሰረተ ፖሊሲን ሥራ ላይ በማዋል የአገልግሎት አሰጣጥና የውሃ ሀብት አስተዳደርን በማሻሻል ዘላቂነት ያለው የውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን ለሁሉም የሚለውን SDG ግብ ለማሳካት ወደ ተግባር ሊለወጡ የሚችሉ 4 ምርምሮችን ለማካሄድ የመግባቢያ ሰነድ ፊርማ በተፈረመው መሰረት የ4 ምርምር ፕሮፖዛሎች ተገምግሞና አማካሪ ቡድን ተቋቁሞ ወደ ሥራ ተገብቷል፣

## 2.5. የድጋፍ አገልግሎት ሥራዎች አፈጻጸም

የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያው 6 ወራት የድጋፍ ዝርዝር ተግባራት ዕቅድ አፈጻጸም በሚከተለው መልኩ ቀርቧል፡፡

### 2.5.1. የፋይናንስና ግዥ ተግባራት አፈፃፀም

- የተለያዩ ክፍያዎች በታቀደው መሰረት ተከናውነዋል፣
- የሂሳብ መዛግብትና የግዥ ሰነዶችን ለኦዲት በሚያመች መልኩ የማደራጀት ሥራ ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት ተሰርቷል፣
- ግዥዎችን ለመፈፀም ታቅዶ የአገልግሎት እና የዕቃ ግዥዎች ተፈፅመዋል፣

**የኦዲት ተግባራት አፈፃፀም**

- የ2013 በጀት ዓመት ፈሰስ ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት በታቀደው መሰረት ሪፖርቱ (100%) ተልኳል፣
- የ2013 በጀት ዓመት የቆጠራ ሥራ ተከናውኗል፣
- የ2013 በጀት ዓመት የ3ኛ ሩብ ዓመት የፋይናንስ ኦዲት ሥራ በማከናወን ሪፖርቱ (100%) ለገንዘብ ሚኒስቴር ተልኳል፣
- የ2013 በጀት ዓመት የ4ኛ ሩብ ዓመት የፋይናንስ ኦዲት ሥራ በማከናወን ሪፖርቱ (100%) ለገንዘብ ሚኒስቴር ተልኳል፣
- 2014 በጀት ዓመት የአንደኛ ሩብ ዓመት የፋይናንስ ኦዲት በመከናወን ላይ ይገኛል፣
- በውስጥና በውጭ ኦዲተሮች ግኝቶች ላይ የክትትል ስራ ለማድረግ ታቅዶ በዚሁ መሠረት ክትትል ተደርጓል፡-
    - የ2012 በጀት ዓመት የውጭ ኦዲት ሪፖርት ላይ የተወሰደ የእርምት እርምጃ እና የድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ ለገንዘብ ሚኒስቴር በወቅቱ እንዲላክ የክትትል ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

### 2.5.2. ንብረትና ጠቅላላ አገልግሎት ተግባራት አፈፃፀም

- የ2013 በጀት ዓመት የአላቂ ዕቃዎች እና የቋሚ ንብረት ቆጣራ ተጠናቋል፣
- የተሽከርካሪ ሥምሪትና ጥገና አገልግሎት አሠጣጥ ተግባራት ተከናውነዋል፣
- የኢንስቲትዩቱ ግቢ ለሥራ ምቹ፣ አረንጓዴና ደህንነቱን በማረጋገጥና በማስዋብ ለሥራ ምቹና ማራኪ እንዲሆን ተደርጓል፣
- በየሳምንቱና በየወሩ ነዳጅ አጠቃቀም ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል በዕቅዱ መሰረት ቀርቧል፣

- ለ4 ተሽከርካሪዎች ጥገና ለማድረግ ታቅዶ ለ3 ተሽከርካሪዎች ጥገና ተደርጎ ሥራ እንዲጀምሩ ተደርጓል፣
- ለ18 ተሽከርካሪዎች የሰርቪስ ሥራ ተከናውኗል፣
- ለ37 ተሽከርካሪዎች የሶስተኛ ወገን ኢንሹራስ ሽፋን እንዲያገኙ ተደርጓል፣

### 2.5.3. የኮሙኒኬሽን ስራዎች አፈፃፀም

- የተቋሙን እንቅስቃሴ የሚጠቁሙ 60 የተለያዩ መልዕክቶችን ቀርጾ ለማስተላለፍ ታቅዶ 69 መልዕክቶች በማኅበራዊ ሚዲያ (ፌስቡክ፣ ትዊተር፣ ብሎግ እና ዩቲዩብ) ተላልፈዋል፣
- የሚዲያ ክትትልና ግብረ-መልስ ለማከናወን ታቅዶ በየቀኑ እና በየሳምንቱ 11 ዋና ዋና ሚዲያዎች ተፈትሸዋል፡፡ በ6 ወራቱ ውስጥ ዘርፉንና ተቋሙን የተመለከቱ የወጡ ዘገባዎች አዎንታዊ ነበሩ፣
- 6 አርቲክሎች በማዘጋጀት በማህበራዊ ሚዲያ ገፆቻችን ለማስተላፍ ታቅዶ 6 አርቲክሎች ተዘጋጅተው እንዲተላለፉ ተደርጓል፣
- የተቋሙን መረጃ በማደራጀት ለመረጃ ፈላጊዎች ለመስጠት 4 የቪዲዮ እና 509 የፎቶግራፍ መረጃዎች በዕቅዱ መሰረት ተደራጅተዋል፣
- 24 ተቋማዊና ሀገራዊ መልዕክቶችን በማዘጋጀት በመሠረተ-ልማት ክላስተር ፌስቡክ ገፅ ‹‹Federal Infrastructure Cluster›› ላይ ለመጫን ታቅዶ 31 መልዕክቶች ተጭነዋል፡፡ በዚህም 74315 ተከታዮች መረጃዎቹን ያዩ ሲሆን 51060 ተከታዮች መረጃዎቹን መሰረት በማድረግ አስተያየቶችን ሲሰጡ በተጨማሪም 3971 ተከታዮች መልዕክቶቹን ለሌሎች አካላት ተደራሽ አድርገዋል፡፡
- 24 የኢንስቲትዩቱን መረጃዎች በመሥሪያ ቤቱ ፌስቡክ ገፅ ‹‹Ethiopian Water Technology Institute›› ላይ ለመጫን ታቅዶ 33 መልዕክቶች ተጭነዋል፡፡ በዚህም 104045 ተከታዮች ሚጃዎቹን ያዩ ሲሆን፣ 27311 ተከታዮች ሚጃዎቹን ማቀረት በማድረግ አስተያየቶችን ሰሰጡ በተጨማሪም 2121 ተከታዮች ሜልዕክቶቹን ለሌሎች አካላት ተደራሽ አደርገዋል፡፡
- 72 ሀገራዊና ተቋማዊ መረጃዎችን በዳይሬክቶሬቱ ዳይሬክተር ፌስቡክ ላይ ለመጫን ታቅዶ 91 መልዕክቶች ተጭነዋል፡፡ መልዕክቶቹን 40274 ተከታዮች ያዩ ሲሆን፣ 25101 ተከታዮች መረጃዎቹን መሰረት በማድረግ አስተያየቶችን ሲሰጡ፣ 19704 ተከታዮች መልዕክቶቹን ለሌሎች አካላት ተደራሽ አድርገዋል፡፡

### 2.5.4. የዕቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ተግባራት አፈጻጸም

- የኢንስቲትዩቱ 2 ዕቅዶች (የ2014 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት መርሃ-ግብር፣ የ2014 በጀት ዓመት ፊዚካል ዕቅድ ለማዘጋጀት ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት ተከናውኗል፣
- የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያውና የሁለተኛው ሩብ ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ለማዘጋጀት በታቀደው መሰረት ተዘጋጅቷል፣
- ሁለት ጊዜ የክትትል፣ የግምገማና ድጋፍ ተግባራትን ተከናውነዋል፣
- 8 የተለያዩ ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎችን ከዓላማ አስፈፃሚ የሥራ ክፍሎች ጋር በመሆን የተዘጋጀ ሲሆን፣ ግብዓት በማሰባሰብ ለማጠናከር የውይይት መድረክ ለመፍጠር በዝግጅት ላይ ነው፣

### 2.5.5. የሥነ-ምግባር ተግባራት አፈፃፀም

- ስምንት ዓይነት የህትመት መልዕክቶችን እና በሥነ-ምግባር የታነፀ አመራር ከሙስና ለፀዳች ኢትዩጵያ የሚል ብሮሸሮችን ለሰራተኞች ማሰራጨት እና የተለያዩ ፖስተሮች መለጠፍ ተችሏል፣
- ዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን በአልን የኢንስቲትዩቱ 88 አመራሮችና ሰራተኞች (ወንድ 46፣ ሴት 42) በተገኙበት በሥነ-ምግባር የታነፀ አመራር ከሙስና ለፀዳች ኢትዩጵያ በሚል መሪ ቃል በስልጠናና ውይይት ማክበር ተችሏል፣
- ሃብት ማስመዝገብ የሚገባቸው ሰራተኞች ዝርዝር 9 (ወንድ 7 ሴት 2) በዕቅዱ መሰረት ለመለየት ተችሏል፣
- በቅድመ-ዳሰሳ ጥናት ለሙስና ተጋላጭ በሆኑ የሥራ ክፍሎች ውስጥ የግዥና ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ላይ ጥናቱን ለመስራት የአሰራር ስርዓት ጥናት የሚያደርግ ኮሚቴ ተዋቅሮ ስልጠናዊ ኦሬንቴሽን በመስጠት ጥናቱን ለማዘጋጀት በዝግጅት ላይ ነው፣
- የሥነ-ምግባር ጉድለት ለሚታይባቸው እና ቅሬታ ለቀረበባቸው 5 ሰራተኞች ምክር ተሰጥቷል፣
- ለ188 (ወንድ 111 ሴት 77) አመራሮችና ሰራተኞች በመልካም ምግባርና ሞራል እሴት ግንባታ እና ሙስና መከላከል ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በዕቅዱ መሰረት ተሰጥቷል፣
- የሥነ-ምግባር ጥሰት ጥቆማ/ቅሬታ 3 ከቀረበው ውስጥ 2 መፍትሄ ያገኘ ሲሆን 1 በሂደት ላይ ነው፣
- ቅሬታ ለቀረበባቸውና የስነ-ምግባር መመሪያ ላይ የግንዛቤ ማነስ ለሚታይባቸው 9 ሰራተኞች ምክር ተሰጥቷል፣

### 2.5.6. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሥራዎች አፈፃፀም

- የኢ.ኮ.ቴ አገልግሎቶችን ለማበልፀግ የ6 ፊዚካል የኢ.ኮ.ቴ መገልገያ ዕቃዎችና የ7 ተቋሙን ለማዘመን የሚረዱ ሲስተሞች ቴክኒካል ስፔሲፊኬሽን ስራ በዕቅዱ መሰረት ተከናውኖዋል፣
- የኢ.ኮ.ቴ መሰረተ ልማት ማስፋፊያ እና ማዘመኛ አዲስ ፕሮጀክት ፕሮፖዛል፡-
    - የዳታ ሴንተር ቴክኒካል ፕሮፖዛል፣
    - የዳታ ሴንተር ባክ አፕ፣
    - ለዳታሴንተር የሚያስፈልጉ አክቲቭ-ዲቫይሶች ስፔሲፊኬሽን በታቀደው መሰረት ተዘጋጅቷል፣
- በተቋሙ አገልግሎት የሚሰጡ ቴክኖሎጂዎች በየጊዜው ደረጃቸው እንዲሻሻል (Upgrade) እየተደረገ ነዉ፡፡

### 2.5.7. የህግ ነክ ጉዳዮች አፈፃፀም

- ለሚቀርቡ ክሶች መልስ ማዘጋጀትና ክርክር ማካሄድ በተመለከተ፡-
    - በኢንስቲትዩቱና በአቶ ዮናስ ተስፋዬ መካከል በነበረ ክስ ለኢንስቲትዩታችን በተፈረደ አግባብ ባለመፈፀሙ አፈጻፀም ተከፍቶ በሂደት ላይ ነው፣
    - የመንግስት ንብረት ያልመለሱ ሁለት ሰራተኞች ንብረቱን ለማስመለስ በሂደት ላይ ነው፣
    - የጠፋውን የተሽከርካሪ መለዋወጫ ክስ ቀርቦ በምርመራ ላይ ይገኛል፣
    - እንስቲትዩቱ የመማሪያ ክፍሎች እድሳት ለማከናወን ውል ከገባው ፕሮጀክት ጋር ተያይዞ እንደውሉ ስላልተፈጸመ እንዲፈጸምልን በከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ ለመመስረት ማስረጃዎችን የማደራጀት ስራ ተሰርቷል፡፡
- የመማሪያ ክፍሎች ዕድሳት ለማከናወን ውል ከገባው ሥራ ተቋራጭ ጋር በውሉ መሰረት ስላልተፈጸመ በከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ ለመመስረት ማስረጃዎችን የማደራጀት ስራ ተሰርቷል፣
- በመ/ቤቱ የሚሰራባቸው አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ሰነዶች ከመንግስት ፖሊሲ ጋር የማይጋጩ መሆናቸውን ማረጋገጥ፡- የፌደራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010፣ ለፌደራል መንግስት ሠራተኞች የዲሲፒሊን አፈጻጸምና የቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት የወጣ የም/ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 77/1994፣ የሥራ ድልድል አፈፀፃም 2008 ዓ.ም መመሪያ የመሳሰሉትን በመታገዝ ለፍ/ቤት መልስ በማዘጋጀትና በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን የማረጋገጥ ስራ ተሰርቶአል፣

### 2.5.8. የሴቶችና ወጣቶች ተግባራት አፈጻጸም

- በትምህርት የሴቶችና ወጣቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ለግል ዩንቨርሲቲዎች ደብዳቤ በመጻጻፍ 50% የክፍያ ቅናሽ ተደርጎላቸው 2 የኢንስቲትዩቱ ሴት ሰራኞች ትምህርታቸውን ለመጀመር በሂደት ላይ ናቸው፣
- 69 ለሚሆኑ ሴት ሰራተኞች የወጣቶች መካተቻ ጋይድ-ላይን ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠና በሰበታ ከተማ ተሰቷቸዋል፣
- ለ35 (ወንድ 15፣ ሴት 20) ባለሙያዎች ስርዓተ-ፆታን በሥራቸው አካተው መስራት የሚቻልበት ሁኔታ ላይ በፌደራል ሴቶችና ህፃናት ሚኒስቴር ባለሙያ የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል፣
- የህፃናት ቀንን ምክንያት በማድረግ ለህፃናት አስፈላጊ የሆኑትን የተለያዩ አልባሳትና ቁሳቁስ ከብር 4000 በላይ የሚገመት በማሰባሰብ እና የገንዘብ ድጋፍ ለካንሰር ህሙማን መርጃ ማዕከል ብር 6,675 ድጋፍ የተደረገ ሲሆን በድምሩ ከ10,000 ብር በላይ ድጋፍ ተደርጓል፣
- የነጭ-ሪቫን ቀንና የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ቀንን ምክንያት በማድረግ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በክፍሉ ባለሙያ በመስጠት በዓሉ ተከብሯል፣
- የተቸገሩ ህጻናትን ለመርዳት ተስፋ አዲስ ፓረንትስ ቻይልድ ሁድ ካንሰር ለሚባል ድርጅት የህፃናት ቁሳቁስና አልባሳት እንዲሁም ከ6000 ብር በላይ የገንዘብ ድጋፍ ተደርጓል፣
- የህፃናት ማዋያ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች የተሟሉ ሲሆን፣ የህፃናት ተንከባካቢ ባለሙያ ቅጥር እንደተፈፀመ ስራ የሚጀመር ይሆናል፣

## 2.6. የበጀት አፈፃፀም

### 2.6.1. መደበኛ በጀት

በዚህ በመጀመሪያው 6 ወራት የታቀደ እና ሥራ ላይ የዋለ በጀት በየፕሮግራምና ንዑስ ፕሮግራም ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

- ለድጋፍ አገልግሎት 8,450,000 ብር ታቅዶ የተመዘገበው አፈፃፀም 8,090,365.97 ብር ነው፡ አፈፃፀሙም በመቶኛ ሲሰላ 96% ነው፡፡

- ለውሃ ቴክኖሎጂ ትምህርትና ስልጠና 4,200,000 ብር ታቅዶ የተመዘገበው አፈፃፀም 4,032,517.00 ብር ሲሆን፣ አፈፃፀሙበመቶኛ ሲሰላ 96% ነው፡፡
- ለምርምር እና ቴክኖሎጂ ሽግግር 4,140,000ብር ታቅዶ የተመዘገበው አፈፃፀም 1,400,541.22 ብር በመሆኑ አፈፃፀሙበመቶኛ ሲሰላ 65% ነው፡፡
- ለብቃት ምዘና አገልግሎትና ድጋፍ 1,655,000 ብር ታቅዶ የተመዘገበው አፈፃፀም 1,625,828.85 ብር ሲሆን፣ አፈፃፀሙ በመቶኛ ሲሰላ 98% ነው፡፡
- ለስፔሻላይዝድ ላቦራቶሪ አገልግሎት 1,370,000 ብር ታቅዶ የተመዘገበው አፈፃፀም 982,381.25 ብር ነው፡ አፈፃፀሙ በመቶኛ ሲሰላ 72% ነው፡፡

በአጠቃላይ የመደበኛ በጀት ዕቅድ 17,815,000 ብር ሲሆን፣ የተመዘገበው አፈፃፀም 16,131,634.29 ብር ነው፡ አፈፃፀሙ በመቶኛ ሲሰላ 91% ነው፡

### 2.6.2. የካፒታል በጀት አፈፃፀም

- ለስፔሻላይዝድ ላቦራቶሪ ህንፃ ግንባታ 14,000,000 ብር ታቅዶ የተመዘገበው አፈፃፀም 3,420,865.54 ብር ነው፡ አፈፃፀሙ በመቶኛ ሲሰላ 24% ነው፡፡
- ለማስተማሪያና ስልጠና ፋሲሊቲ ዕድሳት 9,220,000 ብር ታቅዶ የተመዘገበው አፈፃፀም 4,817,269.74 ብር ነው፡ አፈፃፀሙ በመቶኛ ሲሰላ 52% ነው፡፡
- ለተቋሚዊ አቅም ግንባታ 19,000,000 ብር ታቅዶ የተመዘገበው አፈፃፀም 493,807.21 ብር ነው፡ አፈፃፀሙ በመቶኛ ሲሰላ 3% ነው፡፡
- ለስፔሻላይዝድ ላቦራቶሪ ፈርኒቸርና መሳሪያዎች ግዥ የተመዘገበው አፈፃፀም 4,081,157.14 ብር ነው፡

ለካፒታል ፕሮጀክቶች የተያዘ አጠቃላይ ካፒታል በጀት ዕቅድ 42,220,000 ብር ሲሆን፣ የተመዘገበው አፈፃፀም 12,813,099.63 ብር ነው፡ አፈፃፀሙ በመቶኛ ሲሰላ 30.3% ነው፡

## 3. የማጠቃለያ ምዕራፍ አፈጻጸም

በየደረጃው ያሉ አስፈፃሚዎችና ፈፃሚዎች በዕቅድ አፈጻጸም ወቅት የነበራቸው ሚና፣ የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 3.1. የድጋፍ አሰጣጥ አፈጻጸም

### 3.1.1. የከፍተኛ አመራሩ ጠንካራ ጎንና በእጥረት የታዩ

**ጠንካራ ጎን**

ኢንስቲትዩቱ የተሻለ አፈጻጸም በማስገኘት የሚጠበቀውን ውጤት ለማስመዝገብ በተዘረጋው የክትትልና ድጋፍ መርሃ-ግብር መሰረት የተሰሩ ሥራዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ከባለድርሻ አካላት እና የዕርዳታ ተቋማት ጋር በቅንጅት የመስራት ልምድ እየተጠናከረ መምጣቱ፣
- የለውጥ ስራዎች በባለቤትነት በመምራት ሶስቱ የማስፈፀም አቅም ገፅታዎች /የሰው ኃይሉን የማሰልጠንና የማብቃት ስራ፣ አሰራሮችንና አደረጃጀቶችን የማስተካከል ስራ እና የለውጥ ማሳኪያ መሳሪያዎችን በጥምረት ተግባራዊ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑ፣

### 3.1.2. የመካከለኛ አመራር

**ጠንካራ ጎኖች**

- ለፈፃሚው ተግባራትን ቆጥሮ የመስጠትና አፈፃፀሙን የመከታተልና የመመዘን ስራ መስራቱ፣
- በለውጥ ሰራዊት አግባብ ዕቅድን በማዘጋጀት አፈፃፀሙ በባለቤትነት ስሜት እንዲሰራ የማድረግ ሥራ መኖሩ፣
- የፈፃሚውን አመለካከት፣ ዕውቀትና ክህሎት ለመገንባት እና ለማሻሻል ውይይት እየተደረገ መሆኑ፣
- የፈፃሚው የግል ዕቅድ በቢ.ኤስ.ሲ ቅኝት ከተቋሙ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ጋር እንዲተሳሰር መደረጉ፣

**በእጥረት የታዩ ጉዳዮች**

- ግንባር-ቀደሞችን በሚፈለገው መጠን ያለማፍራት፣
- ፈፃሚዎችን ማብቃት ላይ ክፍተት መኖሩ፣
- መረጃዎችን በማደራጀት በወቅቱ ለሚመለከተው መስጠት ላይ ውስንነት መኖሩ፣

### 3.1.3. የለውጥ ቡድንና ፈፃሚን በተመለከተ

**የታዩ ጠንካራ ጎኖች**

- ከተቋም ዕቅድ ጋር የተሳሰረ የግል ዕቅድን በማዘጋጀት ወደ አፈፃፀም መግባት መቻሉ፣
- የሥራ ላይ እርስ-በእርስ አቅም የመገነባባት ስራ መኖሩ፣

**በፈጻሚው የታዩ ደካማ ጎኖች**

- የመንግስት የስራ ሰዓትን የመሸራረፍ ሁኔታ መኖሩ፣
- በአንዳንድ ፈጻሚዎች ዘንድ የጠባቂነት መንፈስ መኖሩ፣

## 3.2. ተቋማዊ ጠንካራና ደካማ ጎኖች

**የነበሩ ጠንካራ ጎኖች**

- በቁፋሮ ቴክኖሎጂ የተፈጠረውን የሥልጠና መሣሪያዎች እጥረትን ለመቅረፍ ከኦሮሚያ እና ከመከላከያ ድሪሊንግ ጋር በቅንጅት መስራት መቻሉ፣
- በስልጠና ላይ ለተሳተፉ ሰልጣኞች ከስልጠና በኋላ የቴሌግራም ፔጅ በመክፈት በቀጣይነት እርስ-በርስ እንዲማማሩ እየተደረገ ይገኛል፣




- የለውጥ ሥራዎችን ሥራ ላይ ማዋል ቁልፍ ተግባር በማድረግ የተሰጠንን ተልዕኮ በሰራዊት አግባብ እንዲሆን መደረጉ፣
- ኢንስቲትዩቱ ተልዕኮውን ለማሳካት እና ተቋማዊ ቁመና ለመያዝ ከመንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ባለድርሻ አካላትና ድርጅቶች ጋር በቅንጅት ለመሥራት እያደረጋቸው የሚገኙ ጥረቶች፣
- ተቋሙ ባለው ውስን የሰው ኃይልና የስልጠና መሳሪያዎች ተልዕኮውን ለማሳካት እያደረገ ያለው ጥረት፣
- በኦዲት ምርመራ ግኝቶች መሠረት የእርምት እርምጃ መወሰዳቸው፣

**የነበሩ ደካማ ጎኖች**

- የአፈፃፀም ውስንነቶችን በመገምገም የአቅም ማጎልበቻ ስልቶችን በመጠቀም የአቅም ግንባታ ሥራዎች በሚፈለገው ደረጃ እየተሰሩ ያለመሆን፣

## 3.3. ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

**ያጋጠሙ ችግሮች**

- የስልጠና መሳሪያዎች እጥረት እና የስልጠና መሳሪዎች ጥገና ላይ የአቅም ውስንነት የሚታይበት መሆኑ፣
- በሙያ ብቃት ምዘና ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በተደጋጋሚ ቢሰጥም የዘርፉ ባለሙያዎች የሙያ ብቃት ምዘና አገልግሎት ለማግኘት ያላቸው ፍላጎት አናሳ መሆን፣
- IFMIS አሰራርን ባለሙያው በደንብ አውቆ መስራት ላይ ችግር ያለ መሆኑና የሲስተም መቆራረጥ ሥራን እያጓተተ መሆኑ፣

- የግዢዎች ሂደት ረጅም በመሆኑ በወቅቱ ያለመፈፀም፣
- አንድ የመቆፈሪያ ማሽን በብልሽት ምክንያት ለረጅም ጊዜ መቆሙ እንዲሁም በውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ሙያ የሙያ ብቃት ምዘና አገልግሎት ለመስጠት የሪግ መቆፈሪያ ማሽን ስርቪስ ለማድረግ ተፈትቶ ሳይጠገን የቆየ በመሆኑና አገልግሎት መስጠት ባለመቻሉ በቁፋሮ ቴክኖሎጂ ሙያ ለመመዘን የተመዘገቡ 26 ባለሙያዎች የሙያ ብቃት ምዘና አገልግሎት መስጠት ያለመቻል፣
- የ "Borehall Camera" የማሰልጠኛ መሳሪያ ያለመጠገን ሥራ ላይ ተፅዕኖ ፈጥሯል፣
- በፀጥታ ችግር ምክንያት ከአማራና አፋር ክልል በተያዘው ዕቅድ መሰረት ሰልጣኞች መምጣት ያለመቻል፣

**የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች**

- የአቅም ውስንነትን ለመፍታት ከሌሎች የትምህርትና ስልጠና እና የዘርፉ ተቋማት ጋር አብሮ ለመስራት ቅንጅት በመፍጠር እና የተለያዩ ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎችን በማዘጋጀት ከለጋሽ ድርጅቶችና መንግስታዊ ተቋማት ሀብት የማፈላለግ ሥራ ተሰርቷል፣
- የሙያ ብቃት ምዘና አገልግሎት አስፈላጊነት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና የአመለካከት ለውጥ እንዲመጣ በተደጋጋሚ እየተሰራ ነው፣
- የ IFMIS ስልጠና ለመስጠት በዝግጅት ላይ ነው፣
- ጥገናዎች እንዲካሄዱ ጥረት እየተደረገ ነው፣

**የበጀት አፈፃፀም በሠንጠረዥ**

**የመደበኛ በጀት አፈፃፀም**

| ተ.ቁ | የፕሮግራም ሥም | የበጀት ዓመቱ ዕቅድ | የሩብ ዓመቱ ዕቅድ | ክንውን | በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሥራ አመራርና ድጋፍ | 16,550,000 | **8,450,000** | **8,090,365.97** | **96%** |
| 2 | ውሃ ቴክኖሎጂ ትምህርት ስልጠና | 8,500,000 | **4,200,000** | **4,032,517.00** | **96%** |
| 3 | ምርምር እና ቴክኖሎጂ ሽግግር | 5,000,000 | **2,140,000** | **1,400,541.22** | **65%** |
| 4 | የብቃት ምዘና አገልግሎትና ድጋፍ | 3,000,000 | **1,655,000** | **1,625,828.85** | **98%** |
| 5 | ስፔሻላይዝድ ላቦራቶሪ አገልግሎት | 2,950,000 | **1,370,000** | **982,381.25** | **72%** |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **አጠቃላይ አፈፃፀም** | 36,000,000 | **17,815,000** | **16,131,634.29** | **91%** |

## የካፒታል በጀት አፈፃፀም

| ተ.ቁ | ካፒታል ፕሮጀክቶች | የበጀት ዓመቱ ዕቅድ | ዕቅድ | ክንውን | በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የስፔሻላይዝድ ላቦራቶሪ ህንፃ ግንባታ | 14,000,000 | **9,220,000.00** | **4,817,269.74** | **52%** |
| 2 | የማስተማሪያና የስልጠና ፋሲሊቲ ዕድሳት | 23,000,000 | **14,000,000.00** | **3,420,865.54** | **24%** |
| 3 | ተቋማዊ አቅም ግንባታ | 20,000,000 | **19,000,000.00** | **493,807.21** | **3%** |
| 4 | የስፔሻላይዝድ ላቦራቶሪ ፋርኒቸርና መሳሪያዎች ግዥ | 23,000,000 | **-** | **4,081,157.014** | **22%** |
| አጠቃላይ አፈፃፀም | | 80,000,000 | **42,220,000** | 12,813,099.63 | 30.3 |